መልእክት ሦስት

## በሮሜ 8 ባለው በሕይወት መንፈስ ሕግ
## በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ ውስጥ መኖር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ሮሜ 8፡2፣ 10፣ 6፣ 11፣ 28-29፤ 12፡1-2

**I. ድል ነሺ የመሆኛው ቁልፉ፣ [ለጌታ] አጥብቆ ፈላጊዎች የተጻፈ ምዕራፍ በሆነው በሮሜ 8 ውስጥ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ነው—7፡24—8፡2፣ 28-29፤ መዝ. 105፡4፦**

ሀ. ሮሜ 7 "በሥጋ" የመሆን ልምምድ ነው፤ ሮሜ 8 "በመንፈስ" የመሆን ልምምድ ነው (መለኮታዊው መንፈስ በሰው መንፈሳችን ውስጥ መኖሩ እና እነዚህ ሁለቱ አንድ መንፈስ ለመሆን አብረው መዋሐዳቸው)—ቁ. 4፣ 9-10፣ 16፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ 2 ጢሞ. 4፡22።

ለ. በሮሜ 8 ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ድሰታ ሮሜ 12 ውስጥ ወዳለው የክርስቶስ አካል እውነታ ያስገባናል፤ በአካሉ ውስጥና ለአካሉ ስንኖር ሳለ ይህ ሕግ በውስጣችን ይሠራል—8፡2፣ 28-29፤ 12፡1-2፣ 11፤ ፊልጵ. 1፡19።

**II. ሮሜ 8 የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት እና የአጽናፍ ዓለም ማዕከል ነው፤ ስለዚህ ሮሜ 8ን እየተለማመድን ከሆነ፣ በአጽናፍ ዓለም ማዕከል ውስጥ ነን፦**

ሀ. በጥንት ዘላለም እግዚአብሔር ሕይወታቸው እንዲሆንና እነርሱም ብዙዎች የተካተቱበት መገለጡ እንዲሆኑ ወደ ተዋጀት ሕዝቡ ውስጥ ለመግባት አቀደ፤ ይህ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ትኩረት ነው—ኤፌ. 1፡3-5።

ለ. የእግዚአብሔር ውጥን በሰው በኩል መገለጥ ስለሆነ ሰው የእግዚአብሔር ፍጥረት ማዕከል ነው፤ ሰው የእግዚአብሔር መገለጥ ሊሆን የሚችለው ሰው በእርሱ እንዲኖር እና እርሱን እንዲኖር ጭምር እግዚአብሔር የሰው ሕይወት እና ይዘት ለመሆን እና ሰውን ከእርሱ ጋር አንድ ለማድረግ ወደ ሰው ውስጥ በመግባቱ ብቻ ነው፤ በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ከሰው ውስጥ ይገለጣል።

ሐ. ዘካርያስ 12፡1 "ሰማያትን የዘረጋ፥ ምድርንም የመሠረተ፥ የሰውንም መንፈስ በውስጡ የሠራ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ይላል፦

1. መንፈሳችን እግዚአብሔር ሊኖርበት የሚፈልገው ስፍራ ስለሆነ የሰው መንፈስ ከሰማይና ከምድር ጋር ተመድቧል—ኤፌ. 2፡22፤ ተዛ. 2 ጢሞ. 4፡22።
2. ሰማያት ለምድር ናቸው፣ ምድር ለሰው ናት፣ ሰውም ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝ፣ እግዚአብሔርን እንዲቀበል፣ እግዚአብሔርን እንዲያመልክ፣ እግዚአብሔርን እንዲኖር፣ ለእግዚአብሔር የእግዚአብሔርን አላማ እንዲፈጽም እና ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንዲሆን ከመንፈስ ጋር በእግዚአብሔር ተፈጥሯል።

መ. በአጽናፍ ዓለም ውስጥ ያለው ማዕከላዊ ትኩረት በሂደት ያለፈው ሦስት አንዱ አምላክ ወደ እኛ ውስጥ መምጣቱ እና አሁን በእኛ ውስጥ መኖሩ ነው፤ ይህ ታላቁ ተዓምር ነው፤ በአጽናፍ ዓለም ውስጥ ምንም ነገር ከዚህ የበለጠ አስፈላጊ ሊሆን አይችልም—ኢሳ. 66፡1-2፤ ዮሐ. 14፡23፤ 15፡4።

ሠ. ሦስታንዱ አምላክ በእኛ ውስጥ ስለሚኖር እና ከእኛ ጋር አንድ ስለሆነ ሁላችን በደስታ የተሞላን ልንሆን ይገባል፤ እርሱ ሕይወታችን እና ማንነታችን ነው፣ የእርሱ መኖሪያም እያደረገን ነው—ኤፌ. 3፡14-17።

ረ. ሦስታንዱ አምላክ እንደ "ሳይንሳዊ" ሕግ፣ ከሰው ቁጥጥር ውጭ እንደሆነ መርህ በመንፈሳችን ውስጥ የተተከለ የሕይወት መንፈስ ሕግ ለመሆን በተሠግዎ፣ በስቅለት፣ በትንሣኤ እና በዕርገት በኩል በሂደት አልፏል፤ ይህ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ ካሉት እጅግ ታላላቅ ግኝቶች፣ ምለሳዎች ውስጥ አንዱ ነው—ሮሜ. 8፡2-3፣ 10-11፣ 34፣ 16።

ሰ. የሕይወት መንፈስ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የክርስቶስ መንፈስ፣ ክርስቶስ ራሱ እና በሮሜ 8፡2፣ 9-11 ያለው በውስጥ የሚያድረው መንፈስ ሁሉም ሕይወት የሚሰጠውን የተቀመመውን መንፈስ ያመለክታሉ—ተዛ. ዘጸ. 30፡22-25፤ ፊልጵ. 1፡19፤ 1 ቆሮ. 15፡45፦

1. *የእግዚአብሔር መንፈስ* በሚለው አገላለጽ ውስጥ፣ *መንፈስ* እና *እግዚአብሔር* አንዱ የሌላው ገላጭ እና አቻ ሆነው ተቀምጠዋል፣ ይህም መንፈስ እና እግዚአብሔር አንድ እንደሆኑ ያመለክታል—ሮሜ 8፡9።
2. በተመሳሳይ፣ በሮሜ 8 ያሉት *የክርስቶስ መንፈስ፣ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ* እና *የሕይወት መንፈስ፣* መንፈስ ክርስቶስ፣ ከሙታን የሚያስነሣው ማንነት እና ሕይወት መሆኑን ያመለክታሉ፤ ስለዚህ፣ መንፈስ በእኛ ውስጥ ስለሚያድር፣ የሦስታንዱ አምላክ ሦስቱም በእኛ ውስጥ እንደ ሕይወት አሉ—ቁ. 9፣ 11፣ 2።

3. በሮሜ 8 ያለው መንፈስ እንደ የሦስታንዱ አምላክ ከፍተኛው-የመጨረሻው-ምርጡ መጠናቀቅ እና ወደ እኛ መድረስ እና መተግበር ሁሉን-ያካተተው መንፈስ ነው።
4. እንደ ሕይወታችን እና ማንነታችን በመውሰድ እንድንለማመደው እና እንድንደሰተው ሦስታንዱ አምላክ ሁሉን-እንዳካተተው መንፈስ በውስጣችን አለ፤ እኛ የሦስታንዱ አምላክ መያዣ ነን—2 ቆሮ. 4፡7።

ሸ. በጌታ በማመን እርሱን ስንቀበል፣ እንደ መለኮታዊው፣ ያልተፈጠረው የእግዚአብሔር ሕይወት (በግሪክ ዞዊ) ራሱን ወደ መንፈሳችን ውስጥ ለማደል እንደ የሕይወት መንፈስ ሕግ አገልግሏል፤ ሁላችንም ቢያንስ አንዱ የማንነታችን ክፍል፣ መንፈሳችን ዞዊ የመሆኑን ታላቅ መገለጥ ማየት ያስፈልገናል፤ አእምሯችንን በመንፈስ ላይ ስናደርግ፣ ነፍሳችንን የሚወክለው አእምሯችን ዞዊ ይሆናል፤ በተጨማሪም፣ ዞዊ በሕይወት መንፈስ ሕግ አሠራር ወደ የሚሞተው ሰውነታችን ውስጥ ሊተላለፍ ይችላል፤ በዚህ መንገድ የዞዊ ከተማ፣ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም እንድንሆን በሦስቱም ክፍላችን በሙሉ የዞዊ ሰዎች እንሆናለን—ራእ. 21፡6፤ 22፡1-2፣ 14።

ቀ. በመጨረሻም፣ ይህ ሕይወት የክርስቶስ ሙሽራ እንድንሆን ያዘጋጀናል፣ ይህም ጌታ ተመልሶ እንዲመጣ እና ወደ ቀጣዩ ዘመን እንዲያስገባን ያደርጋል፤ በዚህ ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስ እና የአጽናፍ ዓለም ወሳኙ ትኩረት በሮሜ 8 ውስጥ ነው።

## III. ሮሜ 8 በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ እንደ የሕይወት መንፈስ ሕግ ለአማኞች ለኑሮአቸው መለኮታዊውን ሕይወት እንደሚሰጣቸው ይገልጣል፤ ይህ የመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ ልምምድ ነው—ቁ. 2፣ 10፣ 6፣ 11፣ 28-29፦

ሀ. ሕይወትን እንደሚሰጠው መንፈስ በመንፈሳችን ውስጥ የተተከለው በሂደት ያለፈው ሦስታንዱ አምላክ ከኤሌክትሪክ ጋር ሊመሳሰል ይችላል፤ እንደ መለኮታዊው "ኤሌክትሪክ" ሕግ በውስጣችን ያለው የእግዚአብሔር አሠራር ይህንን ሕግ በጸሎት "እንድናስነሣው" ትብብራችንን ይጠይቃል—ቆላ. 4፡2፤ ኤፌ. 6፡17-18፤ 1 ተሰ. 5፡17፤ ተዛ. ማቴ. 24፡27 (በእንግሊዝኛው የሪካቨሪ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የግርጌ ማስታወሻ 1 የመጨረሻዎቹን ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተመልከቱ)።

ለ. በጸሎት ጌታን በመንካት ስንቀይ፣ በመንፈሳችን ከእርሱ ጋር በመገናኘት ስንቀይ፣ የሕይወት መንፈስ ሕግ ከሰው ቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ፣ በቅጽበት እና ያለ ጥረት በውስጣችን ይሠራል—ዕብ. 11፡1፣ 5-6፤ 2 ቆሮ. 4፡13፤ ማቴ. 8፡3፣ 15፤ 9፡20-21፣ 29፤ 14፡36፤ 17፡7፤ 20፡34፤ ዮሐ. 4፡23-24፤ ፊልጵ. 2፡12-13፤ ሮሜ 8፡2፣ 4፣ 6፣ 13-16፣ 23፤ 1 ተሰ. 5፡16-18።

ሐ. የጸሎት ትርጉሙ እግዚአብሔርን መምጠጣችን ነው፤ ከእግዚአብሔር ጋር አብልጠን በተገናኘን ቁጥር፣ አብልጠን እንመጠዋለን፤ አብልጠንም ስንመጠው፣ እንደ ብርሃናችን እና መዳናችን አብልጠን እንደሰተዋለን—2 ነገ. 19፡30፤ ኢሳ. 37፡31፤ ማቴ. 6፡6፤ መዝ. 119፡15፦

1. በመዝሙር 27፡1 ዳዊት "እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው" ይላል፤ እግዚአብሔርን እንደ ውበት በትኩረት በመመልከት ከእርሱ ጋር ተገናኘ፣ እግዚአብሔርንም መጠጠ (ቁ. 4)፤ ስለዚህም፣ ብርሃንን እና መዳንን ከውስጥ ተቀበለ።
2. "እንደሆንኩት ሆኜ" የሚል መዝሙር አለ (ከእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ፣ #1048)፤ ይህ ማለት ሁኔታችንን ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ ሳንሞክር እንደሆንነው ሆነን ወደ እግዚአብሔር መምጣት አለብን ማለት ነው፤ ክርስቶስን የተቀበልነው በዚህ መንገድ ነው፣ በክርስቶስ ልንመላለስ የሚገባንም በዚህ መንገድ ነው—ቆላ. 2፡6-7።
3. መጸለይ እንደሆንነው ሆነን ወደ ጌታ መምጣት ነው፤ ወደ ጌታ ስንመጣ፣ የውስጣችንን ሁኔታ በፊቱ ማስቀመጥ እና በሁሉም ነገር እጥረት እንዳለብን መንገር አለብን፤ ደካሞች፣ ግራ የተጋባን፣ ኀዘንተኞች እና የምንናገረው የሌለን ብንሆን እንኳን፣ ወደ እግዚአብሔር መምጣት እንችላለን፤ የውስጣችን ሁኔታ ምንም ቢሆን፣ ያንን ወደ እግዚአብሔር ማምጣት አለብን።
4. ስለ ሁኔታችን በመጨነቅ ፋንታ፣ ወደ እርሱ በመመልከት፣ እርሱን ትኩር ብሎ በማየት፣ እርሱን በማወደስ፣ ለእርሱ ምስጋናን በማቅረብ፣ እርሱን በማምለክ እና እርሱን በመምጠጥ እርሱን ለመገናኘት ወደ መገኘቱ ውስጥ መግባት ያስፈልገናል፤ ያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ብልጥግናዎች እንደሰታለን፣ ጣፋጭነቱን እንቀምሳለን፣ እንደ ብርሃን እና ኃይል እንቀበለዋለን፣ በውስጣችንም ሰላማዊ፣ ብሩህ፣ ጠንካራ እና የበረታን እንሆናለን፤ ከዚያም ቃሉን ለቅዱሳን ስናገለግል ከእርሱ ጋር በመገናኘት የመቆየትን ትምህርት እንማራለን—1 ጴጥ. 4፡10-11; 2 ቆሮ. 2፡17; 13፡3።

*መ.* የጸሎት ትርጉም እግዚአብሔርን መግለጣችንም ጭምር ነው፤ በመዝሙር 27፡4 ዳዊት የያሕዌን ውበት ትኩር ብሎ ማየት ብቻ ሳይሆን በመቅደሱም መጠየቅ እንደሚሻ ጭምር ይናገራል፤ መጠየቅ በጸሎት ለእርሱ የምንናገራቸው ቃላት በእርግጥ በውስጣችን የእግዚአብሔር ንግግር፣ የእግዚአብሔር መገለጦች እንዲሆኑ እግዚአብሔር በውስጣችን እንዲናገር መፍቀድ ነው፡-

1. እውነተኛ ጸሎት እኛ ወደ እግዚአብሔር መምጣታችን፣ እግዚአብሔር በውስጣችን እንዲናገር መፍቀዳችን እና እርሱ የተናገረውን መልሰን ለእርሱ መግለጣችን ነው፡- ""ፊቴን ፈልጉ" ባልህ ጊዜ፤ ልቤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ፊትህን እሻለሁ አለች" (ቁ. 8 አ.መ.ት.)።
2. እግዚአብሔርን በእውነት ስንነካው፣ ስንገናኘው እና ስንመጠው፣ በውስጣችን ይናገራል፤ ከዚያም በውስጣዊ ንግግሩ መሠረት እንጸልያለን፤ መጸለይ በውስጣችን መናገር ይችል ዘንድ ወደ እግዚአብሔር መሄድ፣ እርሱን መገናኘት፣ ወደ እርሱ መቅረብ፣ ከእርሱ ጋር መነጋገር እና እርሱን መምጠጥ ነው፤ ለእኛ በሰጠን ቃላት ወደ እርሱ ስንጸልይ፣ ጸሎታችን እግዚአብሔርን ይገልጣል—ዮሐ. 15፡7።
3. በጸሎታችን የመጀመሪያ ገጽታ ወቅት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ወደ ማድረግ እንገባለን፣ እርሱም ለሥራው ያለውን ሸክሙን ይቀባናል፣ ውጥኑንም ይገልጥልናል፤ የጸሎታችን ሁለተኛው ገጽታ ለሥራው ያለውን ፈቃዱን እና ሸክሙን በተመለከተ በመለመን ጌታን መጠየቅ ነው፤ ያኔ የእግዚአብሔር አብሮ-ሠራተኛ ለመሆን ከእግዚአብሔር ጋር በመተባበር የጸሎትን ዓላማ እናከናውናለን—ኢሳ. 62፡6-7፤ 45፡11፤ ሕዝ. 22፡30፤ ዳን. 9፡2-4፤ 1 ሳሙ. 12፡23፤ 1 ቆሮ. 3፡9፤ 2 ቆሮ. 6፡1።
4. ጥያቄ የማቅረብ ጸሎቶች እግዚአብሔርን ያከብራሉ፤ ዳዊት አብዛኛውን ጊዜ ያሕዌን ይጠይቅ ስለነበር እንዴት መጸለይ እንዳለበት ያውቅ ነበር (1 ሳሙ. 22፡10፤ 23፡2፣ 4፤ 30፡8፤ 2 ሳሙ. 2፡1፤ 5፡19፣ 23)፤ እግዚአብሔር ዳዊትን በነቢዩ በናታን በኩል ከተናገረው በኋላ፣ ዳዊት "በእግዚአብሔርም ፊት ተቀምጦ" (7፡18) ለጌታ "እንደ ተናገርህም አድርግ" ብሎ ነገረው (ቁ. 25)፤ በመቀጠልም ከጌታ ንግግር የተነሣ "ባሪያህ ይህችን ጸሎት ወደ አንተ ይጸልይ ዘንድ በልቡ ደፈረ" ብሎ ለጌታ ነገረው (ቁ. 27)።

*ሠ.* እንደ የሕይወት መንፈስ ሕግ በውስጥ ከሚያድረው፣ ከተገጠመው እና በውስጥ ከሚሠራው እግዚአብሔር ጋር በመነጋገር ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት ለመጠበቅ መተባበር አለብን—ሮሜ 10፡12-13፤ ዘፍ. 13፡18፤ 1 ተሰ. 5፡17፤ ኤፌ. 6፡17-18፤ ፊልጵ. 4፡5-7፣ 12-13፤ መዝ. 62፡7-8።

**IV. ለመንፈስ ውስጣዊ ስሜት ስንጠነቀቅ፣ የሕይወት መንፈስ ሕግ በውስጣችን ይንቀሳቀሳል፤ ሁላችንም ልንማረው የሚገባ የክርስትና ሕይወታችን ምሥጢር በሮሜ 8፡6 ይገኛል፣ ይህም እንደ የሕይወት መንፈስ ሕግ ከክርስቶስ መንፈሳዊ ልምምዳችን ጋር የተያያዘ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅግ አስፈላጊው ቃል ነው— "ስለ *ሥጋ* ማሰብ ሞት ነውና፣ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው"፡-**

*ሀ.* ስለ *ሥጋ* ማሰብ ከ*ሥጋ* ጋር መወገን፣ ከ*ሥጋ* ጋር መተባበርና ከ*ሥጋ* ጋር መቆም ማለት ነው፤ ስለ መንፈስ ማሰብ ለመንፈስ መጠንቀቅ፣ ከመንፈስ ጋር መወገን፣ ከመንፈስ ጋር መተባበር እና ከመንፈስ ጋር መቆም፣ ማለትም፣ ለመንፈሳችን ትኩረት መስጠት ማለት ነው—ሚል. 2፡15-16።

*ለ.* ለመንፈስ ውስጣዊ ስሜት ስንጠነቀቅ፣ ውስጣዊውን የሕይወት እና የሰላም ስሜት ስንከተል፣ ለጌታ ልዩና ብቸኛ እንቅስቃሴ እንደ የአካሉ ራስ ጌታን እያከበርነው ነው፤ በወንጌል አገልግሎቱ ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ምርኮኛ ነበር፣ በውጫዊ ከባቢ ሁኔታው ሳይሆን "መንፈሴ ዕረፍት" አግኝቷል ወይም አላገኘም በማለት የሚመራ ነበር (2 ቆሮ. 2፡13)፤ መንፈሱ ከሁሉ ይልቅ ቀዳሚ ሥፍራ የሚሰጠው ክፍሉ ነበር፣ እናም በተዋሐደው መንፈሱ ቁጥጥር ሥር ይሆን፣ ይገዛ፣ አቅጣጫ ይይዝ፣ ይንቀሳቀስ እና ይመራ ነበር (1 ቆሮ. 2፡15፤ ሮሜ 8፡16፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ 2 ቆሮ. 2፡12-14፣ 7፡5-6)።

**V. በመጨረሻ፣ በውስጥ የሚያድረውን እና ከሰው ቁጥጥር ውጪ የሚሠራውን የሕይወት መንፈስ ሕግ በመደሰት በመለኮታዊው *ሥላሴ* መለኮታዊ እደላ ውስጥ የሆነው ኑሯችን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ግብ—አዲሲቱን ኢየሩሳሌም—ለማሳካት፣ እኛን በሕይወት፣ በባሕርይ እና በመገለጥ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር በማድረግ ግብ በክርስቶስ አካል ውስጥ እና ለክርስቶስ አካል ነው—ሮሜ 8፡2፣ 28-29፤ 12፡1-2፤ 11፡36፤ 16፡27፤ ፊልጵ. 1፡19፤ ተዛ. ገላ. 1፡15-16፤ 2፡20፤ 4፡19፣ 26-28፣ 31።**

*© 2022 Living Stream Ministry*